# በደም የተከበረ የዓለም ሠራተኞች ቀን፤ ሜይ ዴይ

***የ«ያ ትውልድ ተቋም»ን ድረ ገጽ ይፋ መደረግ 1ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ***

"ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ በአራቱም አቅጣጫ የተኩስ ድምጽ አልፎ አልፎ ማስተጋባቱ ታውቋል።...በ22/8/69 ጠዋት ባደረግነው መከታተል...በቀጨኔ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አካባቢ የ31 ተማሪዎች አስከሬን፣ በየካ ወረዳ አሥመራ መንገድ የ42 ተማሪዎች አስከሬን ወድቆ መገኘቱና በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ አንሽነት ተለቅሞ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል መወሰዱን...በ23/8/69 እንደዚሁ በገፈርሳ ወረዳ ሳንሱሲ ከሚባለው አካባቢ የ19 ተማሪዎች አስከሬን በጫካ ውስጥ ተጥሎ በአካባቢው ሕዝብ ስለተገኘ...በ24/8/69 በየካ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የ22 ተማሪዎች አስከሬን ተቀብሮ መዋሉን...ይህን መሰል ድርጊት የተፈጸመው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በክፍለሀገራትም ጭምር መሆኑንም ተጨማሪ መረጃ ደርሶናል።"

"አምቡላንስ መኪና በሽተኛ ማመላለሱ ቀርቶ በቀይ ሽብር ምክንያት የተገደሉትን ሰዎች እያነሳን ወደ ቀብር ቦታ መውሰድ ጀመርን።...ስንደርስ በጥይት የተመታ በላዩ ላይ "ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል" የሚል ፅሁፍ የተለጠፈበት አስከሬን እናገኛለን። በከተማው ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተጥሎ የሚገኝ ሲሆን የሚበዛው መርካቶ፣ ፒያሳ፣ አንበሳ ጋራዥ፣ አካባቢ ነበር። ደርግ ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ ገብተን አስከሬን እናወጣ ነበር። አብዛኛዎቹ እጃቸው ታስሮ ነበር የሚገኙት።...በየከተማው የወደቁትን የምናነሳው ለሊትና በጠዋት ነው። የተወሰነ ጊዜ አስከሬናቸውን ሰው ይመልከተው ተብሎ እስከ ቀኑ 3፡00 እና 4፡00 ሰዓት ድረስ ከቆየ በኋላ የሚነሳበት ጊዜ ነበር።...አስከሬኑን ካነሳን በኋላ ለመቅበር ጴጥሮስ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን እንወስዳለን።...በዚህ ሬሣ ማንሳት ሥራ ላይ እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል ሰርቻለሁ።..."

"በየመንገዱ ሰው መገደል ሲጀምር ማለት በቀይ ሽብር መንግስት ሰውን ሲገድል ማለቴ ነው፡ በዛን ጊዜ ዕረፍት አልነበረንም። ቀን ተሌት ከየከፍተኛው፣ ከቀበሌው፣ ከቤተመንግስት፣ ከየፖሊስ ጣቢያው ከየመንገዱ ከየቦታው ማንሳት ነው።...ሰው በየቀኑ ስለሚገደል ጉድጓድ ቆፋሪ ሰራተኞች...ጎጆ ሰርተው ሲቆፍሩ ውለው እዛው ያድራሉ።...በዛን ጊዜ 24 ሰዓት ሙሉ ምግብ የማንበላበት ጊዜ ነበር።"

"...አንዳንድ ሰዎች በተፈላጊነት እየተጠሩ ከመኖሪያ ቤታቸው ከተወሰዱ በኋላ በማግስቱ አስከሬናቸው የተገኘ አሉ።...አንዳንድ ቤተሰቦች ሬሳውን ፈልገው ካገኙ በኋላ አስከሬኑን ለመቅበር የተጠየቀውን ገንዘብ ከፍለው የሬሳ ሣጥንም ገዝተው ለመቅበር ሲዘጋጁ ተከልክለዋል።"

"ምኒልክ ሆስፒታል አስከሬን ምርመራ ክፍል እሰራለሁ። በአዲስ አበባ ከተማ በቀይ ሽብር ወጣቶች በሚገደሉበት ወቅት ...የአስከሬኑ ብዛት...መናገር አልችልም። ከምድር አንስቶ እስከ ጣራ ድረስ አስከሬን በአስከሬን ላይ ተከምሮ የሚኞቹ ቤተሰቦችም በአስከሬኑ ላይ እየቆሙ ልጆቻቸውን ሲፈልጉ አይቻለሁ።"

"አስከሬን ናቸው ተብለው ከመጡት መካከል ጥቂቶቹ ህይወት እየዘሩ ውሃ! ውሃ! አድኑኝ! በማለትና ሌላም ነገር በመናገር ይለፈልፋሉ።...አንዲት ቀይ ቀጠን ያለች 20 ዓመት የሚሆናትና አንድ ጠይም 20-25 ዓመት የሚሆነው ወጣት...አድኑኝ! ውሃ! ውሃ! ሲሉ ነበር። በተለይ ሴቷ ዶ/ር ፍቅሬን ጥሩልኝ አድኑኝ እያለች ትናገር ነበር።"

በየቀኑ ሁኔታዎች ተለዋዋጭና ፈጣን ናቸው። ትግሉ እጅግ በጣም የረቀቀ በሳል አመራርን የሚጠይቅበት ወቅት ነው። የጠላት ኃይል ተደናግጧል፤ የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቷል። የቤተ መንግስቱን ፈላጭ ቆራጭ ወንበሩን ገና ሳይጠግብ "የሕዝብ መንግስት" ብሎ ነገር የለምና እንዳበደ ውሻ ያገኘውን ሁላ ይነክሳል። ወጣት የተባለ፡ ተማሪ የተባለ እስካልተሸመደመደ ስልጣን ደህና ሰንብች ሊሆን እንደሚችል ከ1968 ዓ.ም. ተመክሮ ቀስሟል። አሁንማ እናቶችና ሴቶች እህቶቻችን ዋናው የትግሉ ምሰሶ ሆነዋል። ሲያበረታቱ፣ ሚስጥርና ሰነዶችን ሲደብቁ፣ "አደፍርስ"ን ቀን እንደመክተፊያ ሲጠቀሙ፤ አሰራሩን ሁላ ተለማምደውታል። የቤት ሠራተኞች የዴሞክራሲያና የሌሎች ሰነዶች ሣጥኖች ሆነዋል። እናቶች ወደ ገበያ/ጉልት የሚሄዱ እየመሰሉ ነጠላቸውን ተከናንበው ዘንቢላቸው በ"ዴሞክራሲያ" ተሞልቶ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ማመላለሱን ተክነውታል። የየአካባቢው ወጣቶች አጥርና ተገን የእናቶች ዑዑታ ኮሚቴዎች ሆነዋል። አባቶች በዴሞክራቲክ ፎረም ገንዘብ ያዋጣሉ፤ "ዴሞክራሲያ" አልወጣችም ወይ ማለት ጀምረዋል። ታዳጊ ሕጻናት

"ዓመት አውደ ዓመት ድገምና ዓመት ድገምና

የላባደሩ ቤት ድገምና ዓመት ድገምና፤ ወርቅ ይፍሰስበት ድገምና ዓመት ድገምና

የባንዳዎች ቤት ድገምና ዓመት ድገምና፤ ቦንብ ይዝነብበት ድገምና ዓመት ድገምና"

በማለት የቡሄ ባህልን ለትግሉ ሰጥተዋል።

የመምህራን ማህበር የሠራተኛው ማህበር ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ሆኗል። ሁሉም ሁሉም

"ላምባገነን መንግሥት ሕዝብን ላልወከለ፤ አይገዛም አይገዛም ሕዝቡ ሳለ እየታገለ"

የየዕለት ዝማሬው ሆኗል። ላብ አደሩ በሀገሬ መብቴን፡ ብዝበዛ ያክትም፡ ለተመጣጣኝ ሥራ ተገቢ ክፍያ፤ መፈክሩን ከፍ አድርጓል። የዴሞክራሲ መብትና የሕዝብ መንግስት ጥያቄ አስተጋቢዎችና ተሸካሚ ወጣቶች ለላብ አደሩ ለአርሶ አደሩና ለሰፊው ሕዝብ ግምባር ቀደም ተሰላፊ ሆነዋል። የቤት አጥሮች የትግሉን መፈክር ይዘዋል፤ ኤሌክትሪክ ገመዶች የትግሉን ዓርማ ያውለበልባሉ፤ ስልክ እንጨቶች ቀረብ ባሏቸው ቁጥር የኢሕአፓን ዓርማ ይረጫሉ። በፋሺዝም ላይ ሳር ቅጠሉ ሳይቀር አድሟል። የደርግ መንግስትና አጃቢ ባንዳዎቹ ቋሚ ተጠሪያቸውን BR ጠምደው ላይ ታች ይራወጣሉ። የሰው ልጅን ደም ማፍሰስ የብርጭቆ ውሃ መድፋት ያክል ቀሏቸዋል። አውሬ ሆነው የሰው ልጅ ቀለባቸው ሆኗል። ለሥልጣናቸው እስከጠቀማቸው ድረስ ወንድምና እህትን ይገድላሉ። ቤተሰብን እስከቤቱ ያጋያሉ። አባትና እናቶች ፊት የልጆቻቸውን አስከሬን ይዘረግፋሉ። በዚህም ካልረኩ ቀሪ ልጆቻቸውን ያሳድዳሉ።

የረኸም ጊዜ መከራና ግፍ፡ ቅጥ ያጣ የጭሰኝነት ሥርዓት፣ ረሃብ ብዙዎችን ሲፈጅ የዘመኑ መኳንንትና ባላባት ላለማየትና ላለመስማት የፈንጠዝያ ከበሮ ሲደልቁ፣ በየጊዜው ለተነሱ መለስተኛ ጥያቄዎች ምላሹ ድብደባ፣ እስርና አፈና ብሎም ግድያ እየሆነ መምጣቱ የሁሉም

ኅብረተሰብ ምሬትና ብሶት ተጠራቅሞ የካቲት 66 በዓጼው የፊውዳላዊ ሥርዓት ላይ ያመጸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብት ጥያቄው፡ የስልጣን ጥያቄውን ከግብ ለማድረስ ከተበታተነ ትግል በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ብሔራዊ ስሜቱን እንደጠበቀ፣ ኢትዮጵያዊነቱን እንዳከበረ ሰንደቅ ዓላማውን እያውለበለበ "ድል በትግል" ያዜመበት፣ ወሳኝ ፍልሚያ የገጠመበት በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ትልቅ ሥፍራ ይዞ ያለው ከየካቲት 66 እስከ ሰባዎቹ መጀመሪያ አንዱ ነበር ሊባል ይቻላል።

ደርግ የየካቲትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አቅጣጫውን አስቶ በሀገርና በሰንደቅ ዓላማ ስም ሕዝብን አፍኖና እረግጦ ለመግዛት ከጅምሩ ሲዘጋጅ ለለውጥ ማህበል የተንቀሳቀሰው የሀገሪቷ ብርቅዬ ትውልድ የህዝብን ብሶት አስተጋቢዎች፤ የሕዝብ ገደል ማሚቶዎች ጩኸትና ፍልሚያ ደርግ ስልጣኑን ሳይጠቀልል ጀምሮ ወጥረው የያዙበት ዘመን። የየካቲት እንቅስቃሴን ሊመራ የቻለና የተዘጋጀ የህዝብ ኃይል አለመኖሩ መሳሪያ ታጣቂው እጅ ስልጣን ብትገባም በተፈጠረው ነባራዊ ሁኔታ በመጠቀም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እራሱን በነሐሴ 1967 ዓ.ም. ይፋ በማውጣት ሕዝቡን የማደራጀትና ትግሉን የመምራት ኃላፊነትን የተረከበ ብቸኛ ፓርቲ ነበር።

ኢሕአፓ መሪው መፈክሩ "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብና የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት" ጥያቄ አድርጎ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ አባላት በተለይ በወጣቱ በኩል ሲያሰባስብ፤ በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ስሙን ተከለ። ተቀባይነትን በአጭር ጊዜ አገኘ። ተማሪው፡ ወጣቱ፡ ሴቶች፡ አዛውንቶች፡ ታዳጊዎች፡ ሠራተኞች አርሶ አደሮች ሁሉም ሁሉም በኢሕአፓ ጥላ ሥር ተሰባሰበ። በ1967 እና 68 በኢሕአፓ የተሰራው ከፍተኛ ድርጅታዊ ሥራ ሚያዝያ 23 ቀን 1968 ዓ.ም. ሜይ ዴይ ክብረ ባህል ላይ ፓርቲው ማንነቱ አሳየ። "ሊነቀነቅ የማይቻል" ሕዝባዊ መሰረት እንዳለው በአደባባይ አስመሰከረ። ፋሽዝም በፋሽስቶቹ ፊት ተወገዘ። ቅርንጫፎቹን ኢምፔሪያሊዝም፣ ካፒታሊዝምና ፊውዳሊዝም  ያደረገው የፋሺዝም ዓጽም ከፍ ብሎ ታየ። የየአካባቢ ጥበቃዎችንና የደርግ ፀጥታ ኃይሎችን ለማለፍ ይቻል ዘንድ የደርግን መፈክር ይዘው አብዮት አደባባይ የደረሱት ሁላ ከውስጣቸው ተገላልጠው ሕዝባዊ መፈክሮችንና የኢሕአፓን ዓርማ ይዘው ብቅ አሉ። ሜይ ዴይ 1968 በደርግና በአጀቧቸው አድርባይ ምሁራን ፊት የኢሕአፓ ክብረ በዓል ሆኖ በታላቅ ድል ተከበረ። "ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነው!" ተስተጋባ። ኢሕአፓ ማንነቱንና የት ሊደርስ እንደሚችል እራሱን ይፋ ባደረገ ሁለት ዓመት ባልሞላው ጊዜ አሳየ። መላ ኢትዮጵያ ሜይ ዴይ 1968 ዓ.ም. ከመላው ዓለም ጋር «ኢንተርናሲዮናል» ዘመረች። ወጣቶች ለኢትዮጵያና ለዓለም ላብ አደሮች የትግል አጋርነታቸውን ለማብሰር፣ ለሕዝቡም መሪ ድርጅቱን ኢሕአፓ ለማስተዋወቅ ቀደም ባሉት ቀናት የተዘጋጁበትን መዝሙሮችና መፈክሮች ከዳር እስከዳር በአንድነትና በተቀናጀ መልክ አደመቁት። ኢሕአፓ ጋለ።

ከአቶ አብዲ አብዱላሂ ያልታደለው ትውልድ እውነተኛ ታሪክ መጽሐፋቸው እንዋስና

“«መሬት ለአራሹ ከታወጀለት

ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋምለት

ነፃነት ነፃነት የምትሹ

ተዋጉለት አትሽሹ»

እያሉ እንደ አሸዋ በዝተው፣ እንደ ከዋክብት አብርተው፣ የሕዝብ ልጆች፣ የላብ አደሩ ልጆች አዜሙለት። «ኢሕአፓ ፓርቲያችን ነው! ፣ የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ» ተስተጋባ።”

በአዲስ አበባ አብዮት አደባባይ፤ የኢሕአፓ አደባባይ ሆነች። የደርግ ባለሥልጣናትና የፀጥታ ኃይሎች ውጥረት ውስጥ ገቡ። ዓይናቸውን ማመን አቃታቸው። ጆሯቸውን ተጠራጠሩ። በንዴት ጦፉ። የተኩስ ሩምታ ተለቀቀ። ማ ወዴት እንደሚሄድ አያውቀውም። መሮጥ፣ መተራመስ። የደርግ ዱላ፣ ሰደፍና አፈሙዝ ያገኘው ላይ አረፈ። ድብደባው ጦፈ። ትርምሱ ቀጠለ። አንዳንዱም እየተያዘ ወታደር መኪና ላይ ይወረወር፣ ይታጎር ጀመር። የጭካኔው እርምጃ ቀጠለ። ሜይ ዴይ 68 በተከበረበት በየትኛውም ክፍለ ሀገርና አደባባይ ተመሳሳይ ትዕይንት ተካሄደ። በየጎዳናዎች የልጆችና የወላጆች የጭንቅ ጩኸት በረከተ። እሥራት…ግርፋት…ሥቃይ። ስብራት…ውልቃት…ደም። ደርግ የተጠማውን ደም ማሳደዱ ቀጠለ። ለዓለም ሠራተኞች ቀን የተከፈለ የመስዋዕትነት ደም።

ቃል በቃል እንደ አብዲ አብዱላሂ ያልታደለው ትውልድ እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ አገላለጽ የሜይ ዴይ 68ን ውጤት ሲገልጸው

“ወጣቱ መስዋዕትነትን አሸተተ። ይህ የመጀመሪያ ጀብዱ የብዙዎችን የትግል ስሜት አረካ። የቀደምት ታጋዮችን ጥሪ አስተጋባ፡ ልቡ ሸፈተ፤ አመፀ

«ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ

እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ …» ተዘመረ።

ዛሬ ቀለም አያንጎራጉርም እንጂ፤ ብዕር አያዜምም እንጂ የወጣቱ ስሜት አሁን እንደሚነበበው ሳይሆን ያኔ እንደሚነደው ነበር።

የደሀ ሕዝብ ማህፀን እንደ እሣት የሚፋጅ ትንታጎችን አፈለቀ። ደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣቱን በተቃዋሚነት መነሳሳት ሲያይ ለጕስቋሎች መታገል ተዐምራዊ ኃይል እንደሚያመነጭ በምሬት ተገነዘበ። እነዚህን ለጋ የነፃነት ታጋዮች ሞት ደግሶ ማጉረስ እንዳለበት አመነ።”

ደርግ፡ የኢሕአፓ መሰረትና የወጣቱ የለውጥ ፍላጎት በዚህ ከቀጠለ ደርግ በጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ሊተካ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ገደብ የዴሞክራሲ መብቱን ሊቀዳጅ ነውና ይህን ሕዝባዊ ድል የሕዝብ ልጆችን በማደን፣ በማሳደድ፣ በማሰር፣ በማሰቃየት፣ በመግደል ፋሽታዊ "ድል በድል" ቀረርቶውን ለማላዘን የሞት መጋዙን ደገነ። በሜይ ዴይ 68 ማግስት የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በሚል ስያሜ ገዳይና አራጅ ተቋሙን በመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) መሪነት 1969 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ አቋቋመ። በማስከተልም በኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. የቀድሞ የዓፄ ኃ/ሥላሴ ባለስልጣናትን በድንገት በመግደል በደም የተጨማለቀው ደርግ በጥቅምትና ኅዳር ወር 1969 ዓ.ም. በመግለጫ የ14 ዓመቱ ባቢሌ ኃ/ሥላሴን ጨምሮ 23 እና 27 ወጣቶችን በየተራ ረሸነ።

ይህ እርምጃ ደርግና መኢሶን ሊያካሂዱ ላቀዱት የቤት ለቤት አሰሳ ቀደምት የማሸበሪያ ደወል ነበር። በ1969 ጥር 26 ቀን መንግሥቱ ኃ/ማርያምና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ቀጣይ ውጥን መሠረት የደርጉ ሊቀመንበር የነበሩትን ብርጋዴል ጀነራል ተፈሪ ባንቴንና ሌሎች የደርግ አባላትን በመሰሪ ወጥመዳቸው በመግደል ዋናውን የደም ጥማቱን ለማርካት ደም በተሞላ ጠርሙስ ውርወራ አረመኔው መንግስቱ ኃ/ማርያም በሀገርና ሕዝብ ላይ አጓራ። ቅድመ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ዝግጅት የቤት ለቤት አሰሶ መደምሰስ ዕቅዱ በመኢሶን የበላይ ተቆጣጣሪነት ተግባራዊ ሆነ። የመጀመሪያው ህዳር 1969 ዓ.ም. ሲሆን ሁለተኛው ለሦስት ቀን የተካሄደው መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. የተጀመረው ሲሆን ሶስተኛውና የመጨረሻው ሚያዝያ 1969 የተካሄደውና መኢሶንም እራሱ የወጠነው ጥቃት ሰለባ የሆነበት አሰሳ ነበር።

በነዚህ ተከታታይ አሰሳዎች ኢሕአፓ በ1969 ምርጥ ልጆቹንና መሪዎቹን አጣ። መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ፣ ሻምበል ሞገስ ወ/ሚካኤልና ሌሎች የደርግ አባላት ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. በግፍ ተገደሉ። መኢሶን ያቀደውን አሰሳ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በመሄድ ለማሳለፍ ቃሊቲ ፍተሻ ኬላላይ መጋቢት 4 ቀን 1969 ዓ.ም. የተገደሉት ዮሐንስ ብርሃኔና የኢሕአፓው አባል ብሪታኒያዊው ዶር ዊልያምስ ሄስ ሞርተን፣ መላኩ ማርቆስ፣ የዩንቨርስቲ መምህሩ ነጋ አየለ ይገኙበታል። መጋቢት 14 ቀን 1969 ዓ.ም. የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ባልደረባ፤ የስምንት ልጆች እናትና የስምንት ወር ነፍሰጡር ሕይወቷን ለትግሉ የሰጠችው ዳሮ ነጋሽ በግፍ ተገደለች። ዶር ተስፋዬ ደበሳይና በሪሁን ማርዬ መጋቢት 15 ቀን 1969 ዓ.ም.፣ አንጋፋው የሠራተኛው መሪ ማርቆስ ሀጎስ መጋቢት 17 ቀን 1969 ዓ.ም. በደርግ አሳሾች እጅ ላለመውደቅ ተታኩሶ በመጨረሻም እራሱን የሰዋ፣ የኢሕአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው ክፍሉ ተፈራ፣ የኢሕአፓ ፖለቲካ ዘርፍ አባል ሙሉጌታ ዜና እና በወታደራዊው አገዛዝ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራና ተቀባይነት የነበረው የፖሊስ ሠራዊት ባልደረባ፤ የጭቁን ወታደሮች ሊቀ መንበር ጀግናው ሻምበል አምሃ አበበ 1969 ዓ.ም. ሚያዝያ ወር መጨረሻ በግፍ ከተገደሉት ከብዙዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

የዛሬ 36 ዓመት አርብ ሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በመላዋ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ዓለም አቀፍ የሠራተኞችን ቀን፡ ሜይ ዴይ ምክንያት በማድረግ አባላቱና ደጋፊዎቹ በየአካባቢያቸው በሰላማዊ ሰልፍ የተነሱበትን ዓላማ በማስተጋባት የትግል አንድነታቸውን ለመግለጽ ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ለሰልፍ ተንቀሳቀሱ።

ዓለም አቀፍ የላብ አደሩን ቀን ሜይ ዴይ 1969 ዓ.ም. ከደርግ ልቅ ያጣ ጭፍጨፋ አንፃር በዕለቱ ማክበር እንደማይቻል የተገነዘበው ኢሕአፓ፡ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢትዮጵያ ሀገሩና ለጭቁን ሕዝቦች ያለውን ታማኝነትና የዓላማ ጽናትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የሚያዝያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. ሰልፍ ከድርጅቱ እየከዱ ወደ ደርግ መግባት በጀመሩ አንጃዎች ሙሉ መረጃ ለደርግ በመድረሱ መንግሥቱ ኃ/ማርያምና ጀሌዎቹ አብዮት አደባባይ በምሳሌነት ያፈሰሱትን ደም ሊጠጡ ቋምጠውና አድፍጠው ተጠባበቁ።

ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች "ፍጹም ነው እምነቴ" እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። አዲስ አበባ የደም ጐርፍ አጥለቀለቃት። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች ሽብር ሆነ። ማ ይሙት ማ ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፡ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፡ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፡ እናቶች አባቶች ሀዘን፡ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው። አስፋልቶች በወጣቶች ደም ታጠቡ። ልክ የዛሬ 36 ዓመት። በደም የተከበረ የዓለም ሠራተኞች ቀን።

ደርግ አንድ ብርቅዬ ትውልድ ጨረሰ። ሀገሪቷ በድህነት አቅሟ ለልማትና ለዕድገት የኮተኮተቻቸው ልጆቿን ደርግ በላ። ለሕዝብ መብትና ነፃነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ጀግኖች ልጆቿን፤ እምቡጥ አበባዎቿን ኢትዮጵያ ተነጠቀች። ኢትዮጵያዊነት ኩራቷን መለያ ክብሯን ጥቁር ድባብ አጠላባት። እምቢኝ ለመብቴ፤ እምቢኝ ለሀገሬ፡ እምቢኝ ለሕዝቤ ያለ ትውልድ በጥይት ተለቀመ። እየታነቁ ተገደሉ። በቁማቸው ከገደል አፋፍ ተወረወሩ። ወደ ባህር ተጣሉ። ሕጻናት ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እያዩ እንዲያድጉ ተደረጉ። የዚህ አረመኔ አገዛዝ ጦስ ለዛሬም ተርፎ ብሔራዊ ስሜት እተሸረሸረበት፤ ያባት የእናቶቻችን ጀግንነት ተረት እሆነበት ጊዜ ላይ አድርሶናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ልክ የዛሬ ዓመት ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው መብት ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን ለሰዉት የኢትዮጵያ ጀግኖችና የያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያነት በያ ትውልድ ስም ያ ትውልድ ድረ ገጽን (www.yatewlid.com www.yatewlid.org ) ለሕዝብ ይፋ ያደረግንበትን ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. አንደኛ ዓመት ስናከብር ታሪካችን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በሩን ከፍተናልና በታላቅ ደስታ ነው። ዛሬ አጠገባችን የሌሉትን ወንድምና እህቶቻችንን ቢያንስ ስማቸውንና ምስላቸውን እንደያዘ ሚተላለፍ በየትም ሀገርና ቦታ ሆነው የሚያዩት ሐውልት አቁመንላቸዋልና ከተቀበልነው ንስሃ ጠብታዋን በማድረጋችን፡ በመጀመራችን እየተደሰትን ከፊታችን የተደቀነውን ከባድ ኃላፊነት በትጋትና በሙሉ ስሜት ለመወጣት ቃል በመግባት ነው። አብረን ተሰልፈን፡ አብረን ጮኸን፡ አብረን ታግለን፡ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፡ ልናስባቸው ይገባል። እኛ ልንኖር እነሱ ሞተዋል። ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም" "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም" እየፈከሩ፡ "ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት" እየዘመሩ፡ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፡ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፡ ደማቸው ደማችን ነውና፡ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት በመውሰድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆችና ሕዝባችን! ከጎናችን ሳትለዩ ላበረታታችሁን የያ ትውልድ ወገኖችና አካላት፤ በተለያየ ወቅት ትብብር ላደረጋችሁልን የሚዲያ፤ የድረ ገጽ ወገኖችና በጠንካራ መሰረት በመሰባሰብ እዚህ ላደረሳችሁት የ«ያ ትውልድ ተቋም» አባላት በሞላ የዓለም ሠራተኞችን ቀን ሜይ ዴይ 2004 ዓ.ም.ን ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ላደረግነው ያ ትውልድ ድረ ገጽ አንደኛ ዓመት ክብረ በዓልና ዝክረ ሰማዕታት ቀናችን እንኳን በደህና አደረሳችሁ እንላለን።

<<ያ ትውልድ ተቋም>>

ሚያዝያ 23 ቀን 2005 ዓ.ም. (May Day 2013)

ዋቢ ጽሁፎች፡

- «ያልታደለው ትውልድ» እውነተኛ ታሪክ፤ አብዲ አብዱላሂ
- «ያ ትውልድ» ቅጽ II እና III ክፍሉ ታደሰ፤ 1991 ዓ.ም. ኢንዲፔንደንት አሳታሚዎች ሰሜን አሜሪካ
- «ደም ያዘለ ዶሴ» የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት፤ ጥር 2002 አዲስ አበባ

<<ያ ትውልድ ተቋም>> ኢሜል፡ yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com